የሰ.መ.ቁ.136047

የካቲት 26 ቀን 2010 ዓ.ም

ዳኞች፡- 1. ዳኜ መላኩ

2. ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

3. ቀነዓ ቂጣታ

4. ተሾመ ሽፈራዉ

5. ፀሐይ መንክር

አመልካች፡- ጃይንት ኤግልስ ኃ/የተ/የግ/ማህበር- ጠበቃ አቶ ኤርሚያስ አያሌው

ተጠሪዎች፡- 1. ወጋገን ባንክ - ነ/ፈጅ ሙሉ ላቀው ቀርበዋል

2.ጥቁር አባይ ኮንስትራክሽን አ.ማ - ሒሳብ አጣሪ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ - ነ/ፈጅ አቶ ኤልያስ የሺ ጥላ -ቀርበዋል።

ይህ መዝገብ የተቀጠረዉ ለምርመራ ሲሆን ተመርምሮ የሚከተለዉ ፍርድ ተሰጥቷል።

<u>ፍ ር ድ</u>

ይህ የሰበር ጉዳይ የጉዳት ኪሳራ የሚመለከት ሲሆን ለዚህ ችሎት ሊቀርብ የቻለዉ የአሁን አመልካች የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.በመ.ቁ.125574 ጥቅምት 17 ቀን 2009 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልን በማለት ያቀረበዉን የሰበር አቤቱታ መርምሮ ለመወሰን ነዉ።

የጉዳዩ መነሻ ሲታይ በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት የአሁን አመልካች ከሳሽ፣ የአሁን 1ኛ ተጠሪ ደግሞ ተከሳሽ እና የአሁን 2ኛ ተጠሪ ጣልቃ ገብ ሁኖ ሲከራከሩ ነበር። ከሳሽ ባቀረበዉ ክስ ተከሳሽ በሐራጅ የሸጠልንን ቤት 10 ወር ዘግይቶ ያስረከበን ስለሆነ በወቅቱ የገበያ ዋጋ ቤቱን አከራይተን እናገኝ የነበረዉን ገቢ ያሳጣን ስለሆነ በአጠቃላይ ብር 2,900,000 የጉዳት ኪሳራ እንዲከፍለን በማለት ከሷል።

በዚህ ክስ ላይ ተከሳሽ ባቀረበዉ መልስ ተከሳሽ ቤቱን በወቅቱ ለከሳሽ ማስረከብ ያልቻለበት ምክንያት ተበዳሪዉ የጥቁር አባይ ኮንስትራክሽን አ.ማ ሂሳብ አጣሪ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ባለአደራ ቦርድ ሽያጭ እንዲፈርስልኝ በማለት ክስ አቅርቦ በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት፣ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት እና የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሲንከራከር የቤቱ ርክክብ እንዳይፈጸም እግድ ትዕዛዝ በማሰጠቱ ስለሆነ ተከሳሽ የፈጸመዉ ቸልተኝነት ስለሌለ ኪሳራ ለመክፈል ኃላፊነት የለብንም፣ቤቱም ከሳሽ በጠቀሰዉ ገንዘብ መጠን አይከራይም በማለት ተከራክሯል። ጣልቃ ገብ በበኩሉ ባቀረበዉ ክርክር ቤቱ የተሸጠዉ ከሕግ ዉጭ ስለነበር ሽያጩ እንዲፈርስ ከፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት እስከ የፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት ተከራክረን የፌዴራል ሰበር ሰሚ ችሎት ክሳችንን ዉድቅ ያደረገ ቢሆንም፣ ፍ/ቤቶቹ ጉዳዩን እስከሚያጣሩ ድረስ የእግድ ትዕዛዝ መስጠታቸዉ የጣልቃ ገብ ጥፋት ስላልሆነ ካሳ ለመክፈል አንገደድም፣ ክስ ማቅረብና እግድ ማሰጣት ሕገ መንግስታዊ መብት ነዉ፣ ቤቱን ከሳሽ በጠቀሰዉ ገንዘብ መጠን አይከራይም፣ ስለሆነ ክሱ ተቀባይነት የለዉም በማለት ተከራክሯል።

ከዚህ በኋላ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን በመመርመር በሰጠዉ ዉሳኔ ተከሳሽ ቤቱን ለከሳሽ በወቅቱ ማስረከብ ያልቻለዉ በፍ/ቤት ትዕዛዝ እስከተረጋገጠ እና እስካልተካደ ድረስ፣ ተከሳሽ የእግድ ትዕዛዝ በማለፍ ቤቱን የሚያስረክብበት ሁኔታ ስለሌላ፣ ጣልቃ ገብም ቢሆን መብቱን ለማስከበር በማሰብ ክስ አቅርቦ ፍ/ቤቱ ጉዳዩን አጣርቶ ዉሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ ርክክብ እንዳይፈጸም ያደረገ በመሆኑ የጣልቃ ገብ ቸልተኝነት ወይም ጥፋት ነዉ ሊባል አይችልም፣ ተከሳሽም ሆነ ጣልቃ ገብ ኃላፊነት የለባቸዉም በማለት ክሱን ዉድቅ በማድረግ ወስኗል።

የሥር ከሳሽ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ያቀረበ ሲሆን ፍ/ቤቱ ግራ ቀኙቸዉን በማከራከር በሰጠዉ ዉሳኔ በዚህ ጉዳይ የሥር ተከሳሽ ኃላፊነት የለበትም መባሉ በአግባቡ ነዉ፤ ነገር ግን የሥር ጣልቃ ገብ ያለ አግባብ ክስ በማቅረብ የቤቱ ርክክብ እንዳይፈጸም ያሳገደ በመሆኑ በዚህ ምክንያት ከሳሽ ላይ ለደረሰዉ የጉዳት ኪሳራ ኃላፊ የማይሆንበት ምክንያት የለም፤ የጉዳት ኪሳራዉን ልክ በትክክል ለማወቅ ስለማይቻል በርትዕ የሥር ጣልቃ ገብ ብር 900,000 /ዘጠኝ መቶ ሺህ/ ለከሳሽ እንዲከፍል በማለት ወስኗል። የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበዉ በዚህ ዉሳኔ ቅር በመሰኘት ለማስቀየር ነዉ።

የአሁን አመልካች በ1/5/2009 ዓ.ም የተጻፈ አቤቱታ፣ የአሁን 1ኛ ተጠሪ በጨረታ የሸጠዉን ቤት ዘግይቶ ያስረከበ በመሆኑ በአመልካች ላይ የገንዘብ ጉዳት መድረሱ ተረጋግጦ እያለ 2ኛ ተጠሪን ወክሎ ስለሸጠ የጉዳት ኪሳራዉን የመክስ ኃላፊነት የለዉም መባሉ እና የጉዳት ኪሳራዉን በርትዕ መወሰኑ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ እንዲታረምልን በመዘለት በዝርዝር ተከራክሯል።

ይህ ችሎት ጉዳዩን በመመርመር አቤቱታዉ ያስቀርባል በማለት ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡ ባዘዘዉ መሰረት 1ኛ ተጠሪ ግንቦት 11 ቀን 2009 ዓ.ም የተጻፈ መልስ እና 2ኛ ተጠሪ በ14/9/2009 ዓ.ም የተጻፈ መልስ አቅርቧል። የአሁን 1ኛ ተጠሪ መልስ በአጭሩ፣ በዚህ ጉዳይ የሥር ፍ/ቤቶች ተጠሪ ኃላፊነት የለበትም በማለት የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ያልተፈጸመበት ስለሆነ አመልካች ያቀረበዉ አቤቱታ ዉድቅ ሆኖ ወጪና ኪሳራ የመጠየቅ መብት እንዲጠበቅልን በማለት በዝርዝር ተከራክሯል። የአሁን 2ኛ ተጠሪ ባቀረበዉ መልስ በአጭሩ፣ በዚህ ጉዳይ የፍ/ቤቶች ተጠሪ ለደረሰዉ የጉዳት ኪሳራ ኃላፊነት ሳይኖርበት ኃላፊነት አለበት በማለት የሰጡት ዉሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ ኃላፊነት ያለበት 2ኛ ተጠሪ ስለሆነ 1ኛ ተጠሪ በነጻ እንዲንሰናበት በማለት በዝርዝር ተከራክሯል። የአሁን አመልካች የመልስ መልስ አቅርቧል።

የጉዳዩ አመጣጥ ከላይ የተመለከተዉ ሲሆን ይህ ችሎት የግራ ቀኙቸዉን ክርክር አግባብነት ካላቸዉ የሕግ ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ መርምሮታል። እንደመረመርነዉ በዚህ ጉዳይ ሚላሽ ማግኘት ያለበት ጉዳይ ‹‹የአሁን ተጠሪዎች ኃላፊነት የለባቸዉም ተብሎ በዚህ ችሎት ዉሳኔ እስከተሰጠ ድረስ በዚህ መዝገብ ኃላፊነት አለባቸዉ ማለት የሚቻል መሆን አለመሆኑን?›› እንደጭብጥ በመያዝ እንደሚከተለዉ መርምነዋል። በዚህ ጉዳይ የአሁን 2ኛ ተጠሪ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጠዉን ዉሳኔ በመቃወም የሰበር አቤቱታ ለዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርቦ ችሎቱም ግራ ቀኙቸዉን በማከራከር በሰ.መ.ቁ.134438 ህዳር 29 ቀን 2010 ዓ.ም በሰጠዉ ዉሳኔ በዚህ ጉዳይ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.125574 ጥቅምት 17 ቀን 2009 ዓ.ም የሰጠዉ ዉሳኔ በመሻር፣ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.134137 ጥር 25 ቀን 2008 ዓ.ም የሰጠዉን ዉሳኔ በማጽናት ወስኗል። ከዚህ ዉሳኔ መገንዘብ እንደሚቻለዉ

ለክርክር ምክንያት የሆነዉን የቤት ቁጥር 555 ለአመልካች በወቅት ባለማስረከብ ወይም ርክክብ በመዘግየቱ አመልካች ደርሶብኛል ያለዉን የጉዳት ኪሳራ ለመክፈል የአሁን ተጠሪዎች ኃላፊነት የለባቸዉም ተብሎ መወሰኑን ያመለክታል። ይህ ከሆነ ደግሞ የአሁን ተጠሪዎች በዚህ ጉዳይ ለአሁን አመልካች የጉዳት ኪሳራ ለመክፈል ኃላፊነት የለባቸዉም ተብሎ አስቀድሞ ዉሳኔ እስከተሰጠ ድረስ ይህ ጉዳይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.5 (1) መሰረት በፍርድ ያለቀ በመሆኑ፣ አሁን ደግሞ በዚህ መዝገብ ኃላፊነት አለባቸዉ ወይስ የለባቸዉም? ተብሎ ጭብጥ ተይዞ ተመርምሮ ዉሳኔ የሚሰጥበት የሕግ አግባብ የለም። ይህም ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በግራ ቀኙቸዉ ክርክር ላይ ፍርድ በመስጠት ጉዳዩን የቋጨዉ ስለሆነ የሰበር አጣሪ ችሎት ከኃላፊነትና የጉዳት ካሳ መጠን በርትዕ ስለመወሰኑ እንዲጣራ እንደጭብጥ በመያዝ የሰበር አቤቱታዉን በማስቀረብ ግራ ቀኙቸዉ በጽሁፍ ክርክራቸዉን ያጠናቀቁ ቢሆን ከፍ ሲል በተመለከተዉ መሰረት ይህ ችሎት በሌላ መዝገብ ላይ በሰጠዉ ፍርድ ተጠሪዎች ኃላፊነት የለባቸዉም ተብሎ ዉሳኔ እስከተሰጠ ድረስ ድጋሚ ታይቶ ዉሳኔ የሚሰጥበት አግባብ ባለመኖሩን በዚህ ምክንያት የሰበር አጣሪ ችሎት የያዘዉን ጭብጥ አልፎታል ብለናል።

ሲጠቃለል የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የሰጠዉ ዉሳኔ ከዚህ ቀደም ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት በመሻር ተጠሪዎች ኃላፊነት የለባቸዉም በማለት ዉሳኔ የሰጠበት ስለሆነ አሁን ድጋሚ የሚታይበት አግባብ ስለሌለ የሚከተለዉ ተወስኗል።

<u>ዉ ሳ ኔ</u>

1. ይህ ሰበር ሰሚ ችሎት ከዚህ ቀደም በሰ.መ.ቁ.134438 ህዳር 29 ቀን 2010 ዓ.ም በሰጠዉ ዉሳኔ. የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.125574 ጥቅምት 17 ቀን 2009 ዓ.ም የሰጠዉን ዉሳኔ በመሻር፣ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ.134137 ጥር 25 ቀን 2008 ዓ.ም የሰጠዉን ዉሳኔ በማጽናት የወሰነ በመሆኑ፣ ይህ ጉዳይ በፍርድ ያለቀ ጉዳይ በመሆኑ የአሁን አመልካች ባቀረበዉ አቤቱታ መሰረት ድጋሚ ታይቶ ፍርድ የሚሰጥበት የሕግ አግባብ ስለሌለ የሰበር አቤቱታዉ ተቀባይነት የለዉም ብለን ዉድቅ በማድረግ ወስነናል።
2. የዚህ ዉሳኔ ግልባጭ ለሥር ፍ/ቤቶች ይድረስ ብለናል።
3. ግራ ቀኙቸዉ በዚህ ችሎት የደረሰባቸዉን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸዉን ይቻሉ።

መዝገቡ ተዘግቷል።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት።

ቅ/ሀ